ቁጥር፡-ሕ/ም/ማ/ማ/ዳ/1485.../18

ቀን፡- 29/12/2018 ዓ.ም.

ለአብክመ ገቢዎች ቢሮ

ባህር ዳር

ጉዳዩ፡ የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ. ም. እና በዚህ አዋጅ ማሻሻያ መሰረት ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አስመልክቶ አዋጁ በወጣ በ2 (ሁለት) ዓመት ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮ በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

በዚህም መሠረት ቢሯችሁም በቁጥር ገቢዎችም.ቢ/3.8/265 በቀን 27/11/2018 ዓ.ም. በተጻፈ ሽኝ ደብዳቤ "የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር አገቢ 008/2011 ተብሎ የተገለጸውን እንድንመዘግብላችሁ የላካችሁልን መሆኑ የሚታወቅ ነው።

በእኛም በኩል የተላከልንን ይህን መመሪያ በአዋጁ መሠረት ከተመለከትን በኃላ፣ በክልል ደረጃ "የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር 174/2018 ዓ.ም." በሚል መዝግበነዋል።

በመሆኑም መመሪያውን በተመዘገበው ቁጥር መሰረት ሥራ ላይ እንዲውል እየገለጽን፣ የመዘገብነውን 12 ገጽ መመሪያ በዚህ ሽኝ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክንላችሁ መሆኑን እናሳውቃለን።

ከሰላምታ ጋር

መስፍን መኮነን

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤(ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክት/ል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
  ፍትህ ቢሮ

ቀ/ር

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ

የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር

174/2018 ዓ.ም

በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ በወቅቱ ወይም በአንድ ጊዜ መክፈል ለማይችል ታክስ ከፋይ ገቢዎች ቢሮ ክፍያ ጊዜ ለማራዘም እንደሚችል የተደነገገ በመሆኑ፣

ገቢዎች ቢሮ ታክስ ከፋዮች የክፍያ ግዴታቸውን እንዲወጡ ተገቢነት ያላቸውን ሁኔታዎች በማመቻቸት ድጋፍና እገዛ ማድረግ የሚጠበቅበት በመሆኑ፣

ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ በአንድ ጊዜ መክፈል በማይችልበት ጊዜ የተራዘመ የእዳ መክፈያ ጊዜ ስምምነት በማስገባትና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚስተናገድበትን ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ስለሆነ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር 174/2018 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

1/ "የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ" ማለት ማንኛውም ታክስ ከፋይ በአዋጁ መሠረት የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ወይም በወቅቱ ያልተከፈለ የታክስ እዳን ለመክፈል ጊዜ እንዲራዘምለት ሲያመለክት በታክስ ህጎች በተቀመጠው ጊዜ ገደብ እንዲከፍል የሚሰጥ የክፍያ ስምምነት ነው።

2/ "የክፍያ ጊዜ ስምምነት" ማለት ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ (ታክስ፣ ወለድ እና ቅጣት) በአንድ ጊዜ መክፈል ሳይችል ሲቀር ታክስ ከፋዩ እና ገቢዎች ቢሮ ክፍያው የሚፈጸምበትን ጊዜ እና ሁኔታ በተመለከተ በጽሁፍ የሚያደርጉት ስምምነት ነው።

3/ "የታክስ ከፋዮች ምደባ" ማለት ገቢዎች ቢሮ በሚያወጣው መስፈርት መሰረት የደረጃ ሀ፣ የደረጃ ለ እና የደረጃ ሐ ግብር ከፋዮች የሚስተናገዱበት መምሪያ ወይም ጽ/ቤት ወይም ማእከል ነው።

4/ "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት ታክስ ከፋዩ ሊያስወግዳቸው የማይችለው በተፈጥሮ ወይም በሰዉ ሰራሽ ምክንያቶች የሚከሰት ማለትም በተወሰነ አካባቢ የተነሳ ወይም የተፈጠረ ጦርነት፣ በንግድ ስራ ላይ ጫና የሚፈጥ (እንደ ዝርፊያ፣ ጉርፍ፣ ቃጠሎ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅ፣ ተምች) ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም በታክስ ከፋዩ ጽኑ ህመም ወይም ሞት ምክንያት ታክስ ከፋዩ ያለበትን የታክስ ዕዳ መክፈል አለመቻል ነው።

5/ "ጽኑ ህመም" ማለት የንግድ ስራ እንቅስቃሴውን የሚመራለት የታክስ እንደራሴ የሌለው ግለሰብ ታክስ ከፋይ በታክስ ማስታወቂያ ጊዜ ውስጥ ተንቀሳቅሶ እንዳይሰራ

የሚያደርግና ታክስ ከፋዩ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው ጊዜ ወይም አስታውቆ መክፈል ባለበት ጊዜ ውስጥ በታወቀ የህክምና ተቋም ቢያንስ ለአንድ ወር በሚያስተኛ ወይም መንቀሳቀስ በሚያግድ ህመም ላይ መሆኑ በህክምና ማስረጃ የሚረጋገጥ እክል ነው።

6/ "የታክስ ዕዳ" ማለት እንደአግባቡ በታክስ ህጎች መሰረት በመክፈያ ጊዜው መክፈል ሲገባው ያልተከፈለ ታክስ እና ወለድ እንዲሁም አስተዳደራዊ መቀጫዎችን ይጨምራል።

7/ "ዋስትና" ማለት የታክስ ክፍያ ጊዜ እንዲራዘምለት የጠየቀ ታክስ ከፋይ የታክስ ግዴታውን በዉሉ መሰረት ስለመወጣቱ ገቢዎች ቢሮ ስጋት ያደረበት እንደሆነ ወይም ሀብቱ ከታገደ በኃላ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የሚፈቀድለት ሲሆን በታገደ ሀብት ላይ የተሰጠ ዕግድ ለማንሳት የሚጠየቅ የባንክ ዋስትና ነው።

8/ "የማይነሳ አስተዳደራዊ ቅጣት" ማለት በአስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ መሰረት እንዲነሳ ያልተፈቀደው እና የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነቱ አካል የሆነው ተከፋይ አስተዳደራዊ ቅጣት ነው።

9/ "ከፍተኛ የስጋት ደረጃ" ማለት ታክስ ከፋዩ በግብር ወይም በታክስ ዘመኑ በስጋት መምረጫ መስፈርት መሰረት በልዩ ጥንቃቄ እንዲታይ ወይም ለዝርዝር ታክስ ኦዲት ስራ መመረጥ ያለበት መሆኑን የሚያሳይ የተለየ የሥጋት ደረጃ ነው።

10/ "ያልተከፈለ ታክስ" ማለት በመክፈያ ቀን ወይም ገቢዎች ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 32 የተመለከተውን የታክስ መክፈያ ጊዜ ያራዘመ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ ቀሪ ታክስ ማለት ነው።

11/ "የታክስ ጊዜ" ማለት በታክስ አዋጅ መሰረት የታክስ ማስታወቂያ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ ነው።

12/ "የታክስ ስሌት" ማለት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ፣ በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት፣ የስጋት ታክስ ስሌት፣ የተሻሻለ ታክስ ስሌት፣ አስተዳደራዊ ቅጣት፣ወለድ ወይም በታክስ ህግ መሰረት የሚደረግ ማንኛውም ስሌት ነው።

13/ "አዋጅ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ነው።

14/ "ገቢዎች ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ማለት ሲሆን በየደረጃው እርከን የሚገኙ የገቢ ተቋማትንም ይጨምራል።

15/ "ኃላፊ" ማለት የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይም የሚወክለው የሥራ ኃላፊ ወይም በየደረጃው የሚገኝ የገቢ ጽ/ቤት ኃላፊ ነው።

16/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ፣ደንብ እንዲሁም የታክስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ለገቢዎች ቢሮ በወቅቱ መክፈል ያለበትን ታክስ ወይም የመክፈያ ጊዜው ያለፈበትን ያልተከፈለ ታክስ በአንድ ጊዜ መክፈል በማይችልና የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ በሚጠይቅ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት ስለሚፈቀድባቸው ወይም ስለሚከለክልባቸው ሁኔታዎች

4. የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች

1/ በዚህ መመሪያ መሰረት የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የሚፈቀደው፦

ሀ) ታክስ ከፋዩ የታክስ እዳውን በአንድ ጊዜ መክፈል የማይችል ሲሆን፣

ለ) ታክስ ከፋዩ የታክስ ማስታወቂያ ወይም የታክስ ስሌት ማስታወቂያ በደረሰው ጊዜ በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ዉስጥ የማይገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በከፍተኛ የስጋት ደረጃ የተለየ ወይም ሀብቱ በእዳ የተያዘበት ወይም ሀብቱን ለመሸጥ ግልጽ ጨረታ የወጣበት ታክስ ከፋይ እዳውን ለመክፈል ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ዋስትና ወይም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ቋሚ ሀብት ከሚመለከተው አካል አስገምቶ ዋስትና ሲቀርብ ብቻ ይሆናል።

5. የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች፦

1/ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) በታክስ ማስታወቂያ ጊዜ መከፈል ያለበት የታክስ እዳ ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ ወይም ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ መደረግ ያለበት ሲሆን፣

ለ) ታክስ ከፋዩ አስቀድሞ የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተሰጠው ሆኖ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሳይኖር እዳውን ያልከፈለ ሆኖ ሲገኝ፣

ሐ) የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተጠየቀበት የታክስ እዳ መጠን እንደ ታክስ ከፋዩ አመዳደብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ከተቀመጠው አነስተኛ የገንዘብ መጠን በታች ከሆነ፣

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተገለው እንደተጠበቀ ሆኖ ታክስ ከፋዩ፡-

ሀ) በታክስ ዘመኑ በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ፣

ለ) ለዕዳው ማስከፈያ ሀብት እና ንብረት የታያዘበት ከሆነ፣

ሐ) በእዳው የተያዘበትን ንብረት ለመሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ የወጣበት ከሆነ፣የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የሚሰጠው ለእዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ዋስትና ወይም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ቋሚ ሀብት ከሚመለከተው አካል አስገምቶ ዋስትና ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

6. ለታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ መልስ ስለመስጠት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 እና 5 መሰረት በቀረበ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ ላይ የታክስ ቢሮው የሰጠውን ውሳኔ የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ ማመልከቻው በቀረበ በ14 ቀናት ውስጥ ለታክስ ከፋዩ መሰጠት አለበት፡፡

ክፍል ሦስት

የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት ስለሚፈቅደው አካል፣የመክፈያ ጊዜና አከፋፋሉ

7. የክፍያ ጊዜ ስምምነትን ስለሚፈቅደው አካል እና የጊዜ ገደብ ስለመወሰን

1/ ታክስ ከፋዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ራሱ አስታውቆ የሚከፍለውን የንግድ ትርፍ ግብር መክፈል አለመቻሉን ጠቅሶ ሲያመለክት ጥያቄውን የከተማ ወይም የወረዳ ወይም የክፍለ ከተማ ገቢ ጽ/ቤት ኃላፊ አሳማኝ ምክንያት መሆኑን ሲያረጋግጥ ከ3 ወር ላልበለጠ ጊዜ እንዲራዘምለት ሊፈቅድ ይችላል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ለ 3 የግብር ዘመን ተመሳሳይ ጥያቄ የሚያቀርብ ከሆነ የታክስ እዳ መክፈያ ጊዜ አይራዘምለትም።

8. <u>የታክስ እዳ የመክፈያ ጊዜ ስለመወሰን</u>

ታክስ ከፋዩ የታክስ ማሻሻያ ስሌት ዉሳኔ ማስታወቂያ ደርሶት በዚህ መመሪያ መሰረት የታክስ ክፍያ ማራዘሚያ ጊዜ ስምምነት ውል ሲገባ የዕዳው የመክፈያ ጊዜ የሚወሰነው በሚከተለው አግባብ ይሆናል፡-

1/ የደረጃ ሀ ታክስ ከፋዮች በሚስተናገዱበት የታክስ ጽ/ቤት የታክስ ማሻሻያ ስሌት ዉሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ዋና ታክስ፣ መቀጫ እና ወለድ ዕዳ፡-

ሀ) ከብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ / እስከ ብር 100,000/አንድ መቶ ሺህ/ ከሆነ 3 ወር

ለ) ከብር 100,001/አንድ መቶ ሺህ አንድ/ እስከ 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ/ ከሆነ እስከ 6 ወር፣

ሐ) ከብር 200,001 /ሁለት መቶ ሺህ አንድ/ እስከ 500,000/ አምስት መቶ ሺህ /8 ወር፣

መ) ከብር 500,001/ አምስት መቶ ሺህ አንድ/ እስከ ብር 750,000 / ሰባት መቶ ሺህ/ ከሆነ እስከ 10 ወር፣

ሠ) ከብር 750,000 / ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ/ በላይ ከሆነ 12 ወር የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

2/ የደረጃ ለ ታክስ ከፋዮች በሚስተናገዱበት የታክስ ጽ/ቤት የታክስ ማሻሻያ ስሌት ዉሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ዋና ታክስ፣ መቀጫ እና ወለድ ዕዳ፡-

ሀ) ከብር 5,000/አምስት ሺህ/ እስከ 12,500 /አስራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ/ ከሆነ እስከ 3 ወር፣

ለ) ከብር 12,501 /አስራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ አንድ / እስከ ብር 75,000 /ሰባ አምስት ሺህ/ ከሆነ እስከ 6 ወር፣

ሐ) ከብር 75,001 /ሰባ አምስት ሺህ አንድ/ እስከ ብር 250,000 /ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ/ ከሆነ እስከ 8 ወር፣

መ) ከብር 250,001 /ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ አንድ/ እስከ 500,000 /አምስት መቶ ሺህ/ ከሆነ እስከ 10 ወር፤

ሠ) ከብር 500,000 /አምስት መቶ ሺህ/ በላይ ከሆነ እስከ 12 ወር የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

3/ የደረጃ ሐ ታክስ ከፋዮች በሚስተናገዱበት የታክስ ጽ/ቤት የታክስ ማሻሻያ ስሌት ዉሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ዋና ታክስ፣ መቀጫ እና ወለድ ዕዳ፡-

ሀ) ከብር 1000 (አንድ ሺህ) እስከ 10,000 (አስር ሺህ) ከሆነ እስከ 3 ወር፣

ለ) ከብር 10,001(አስር ሺህ አንድ) እስከ 20,000 (ሃያ ሺህ) ከሆነ እስከ 6 ወር፣

ሐ) ከብር 20,001(ሀያ ሺህ አንድ) እስከ 40,000 (አርባ ሺህ) ከሆነ እስከ 8 ወር፣

መ) ከብር 40,001(አርባ ሺህ አንድ) እስከ 60,000 (ስድሳ ሺህ) ከሆነ እስከ 10 ወር፣

ሠ) ከብር 60, 001 (ስድሳ ሺህ) በላይ ከሆነ እስከ 12 ወር፣ የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

4/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተመለከቱት ሁኔታዎች መሟላቱ ተረጋግጦ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተሰጠው ታክስ ከፋይ ከገቢዎች ቢሮ ጋር የክፍያ ጊዜ ስምምነት እንዲፈርም ይደረጋል፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 በተገለጸው መሠረት የታክስ ዕዳው ዋና ታክስ፣ ወለድ፣ መቀጫ ያካተተ ከሆነ በአስተዳደራዊ መቀጫ አነሳስ መመሪያ መሠረት የማይነሳው መቀጫ መጠን ብቻ ተሰልቶ የውሉ አካል የሚደረግ ሲሆን መቀጫው የሚነሳው በውሉ ውስጥ የተካተተው ዋና ታክስ ፣ወለድና የማይነሳ መቀጫ እንዲከፈል ከተደረገ በኋላ ይሆናል፤

6/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 መሰረት ታክስ ከፋዩ የመጀመሪያ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል ተፈራርሞ ግዴታውን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መወጣት ያልቻለ ሆኖ በድጋሜ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ እንዲሰጠው ከማስረጃ ጋር ጥያቄውን ሲያቀርብ የታክስ እዳ ክትትል ባለሙያ ወይም የግብር አወሳሰን፣አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት አስተባባሪ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለመምሪያ ወይም ለጽ/ቤት ኃላፊ በማቅረብ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፤

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የቀረበለት የሥራ ኃላፊ ማስረጃውን በመመዘን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 በተመለከተው የመክፈያ ጊዜ አሰጣጥ ሥርዓት መሠረት እዳውን እንዲከፍል በድጋሚ ሊፈቅድለት ይችላል፤

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 የተገለጸው ቢኖርም በድጋሜ የክፍያ ስምምነት ውል ተፈራርሞ ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ ሌላ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት ሊፈቀድለት አይችልም።

ክፍል አራት

የማራዘሚያ ጥያቄ አቀራረብ ፣መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና የአፈጻጸም ሥርዓት

9. የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ እንዲፈቀድለት የሚጠይቅ ታክስ ከፋይ ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ፤-

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት በሚገባባቸው የታክስ ዕዳዎች ቢያንስ 25% /ሃያ አምስት በመቶ/ ቅድሚያ ክፍያ መከፈል አለበት፤

2/ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ የቀረበው የታክስ ከፋዩ ሀብት ከተያዘ በኋላ ከሆነ የገቢዎች ቢሮ ጉዳዩን ለማስፈጸም ያወጣቸውን ወጪዎች እና ቢያንስ የታክስ ዕዳውን 25% /ሃያ አምስት በመቶ/ ቅድሚያ ክፍያ መከፈል አለበት፤

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተውን ለማስፈፀም ለታክስ ዕዳ ሀብት የተያዘበት ታክስ ከፋይ ዕገዳው ሊነሳለት የሚችለው ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ዋስትና ወይም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ቋሚ ሀብት ከሚመለከተው አካል አስገምቶ ዋስትና ሲያቀርብ ብቻ ነው፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሱት ቅድሚያ ክፍያ ለመወሰን የስሌት መሠረቱ ዋና ታክስ፣ ወለድና የማይነሳው መቀጫ መጠን ይሆናል፤

5/ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ወይም በፍርድ አፈፃፀም ላይ የሚገኝ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ገቢዎች ቢሮ የታክስ ዕዳ አሰባሰቡን ለመከታተል ያወጣቸውን ወጪዎች በሙሉ እንደ አግባብነቱ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ጋር በቅድሚያ መክፈል ይኖርበታል፤

6/ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሶት በውሳኔው ላይ ባለመስማማት ለደንበኞች አገልግሎት ዋና የስራ ሂደት ቅሬታውን ሲያቀርብ አምኖ የከፈለውን ታክስ ወይም ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅሬታውን ሲያቀርብ የከፈለውን ታክስ የክፍያ

ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት በሚገባበት ጊዜ ለቅድሚያ ክፍያው እና ለቀሪ ዕዳው ተቀናሽ ይደረግለታል፤

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን እና በመክፈያ ጊዜ የሚፈጸመው የአከፋፈሉ ቅደም ተከተል በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 34 መሰረት ይሆናል፤

8/ ቅድሚያ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ላሉት ቀሪ ክፍያዎች የመክፈያ ጊዜው የሚታሰበው ቅድሚያ ክፍያው ከተፈጸመበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን ነው፤

9/ በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተገባበት የታክስ ክፍያ በታክስ ሕጉ መሠረት መክፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ እስከተከፈለበት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው ስሌት መሠረት ወለድ ይከፈልበታል፤

10/ በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ ጠቅላላ መጠን በታክስ ክፍያ ካልተከፈለው ዋና ታክስ ሊበልጥ አይችልም፤

11/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /9/ አፈፃፀም ወለድ የሚታሰበው ባልተከፈለው ወይም በሚቀረው ጠቅላላ ዋና ታክስ ላይ ብቻ ነው፤

12/ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ ወይም ታክሱን የክፍያ ጊዜ ስምምነት ገብቶ በመክፈል ላይ ያለ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 104 መሰረት ታክስን አዘግይቶ መክፈል የሚያስከትለው ቅጣት አይታሰብበትም።

10. <u>በልዩ ሁኔታ የሚሰጥ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ</u>

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5፣ 7፣ 8 እና 9 ላይ የተመለከተው ቢኖርም የየገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይም የሚወክለው የስራ ኃላፊ በልዩ ሁኔታ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፤

2/ በልዩ ሁኔታ የመክፈያ ጊዜ እንዲራዘም የሚቀርቡ ጥያቄዎች የሚቀርቡት ለመምሪያው ወይም ለጽ/ቤቱ ይሆናል፤

3/ መምሪያው ወይም ጽ/ቤቱ ስለ ታክስ ከፋዩ የታክስ አከፋፈል ታሪክና በልዩ ሁኔታ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የጠየቀበት ምክንያት አጣርቶ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለክልሉ የግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት ይልካል፤

4/ የክልሉ የግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ለገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይም ለወከለው የሥራ ሃላፊ አቅርቦ በሚወሰነው መሰረት እንዲፈጸም ለመምሪያው ወይም ለጽ/ቤቱ መልሶ ያስተላልፋል፤

5/ የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይም የወከለው የሥራ ሃላፊ የክፍያ ስምምነት ለገባ ታክስ ከፋይ ያለበትን የእዳ ጫና ከግምት ውስጥ በማስገባት የቅድሚያ ክፍያውን እስከ 15 በመቶ ዝቅ ሊያደርግ ይችላል።

11. የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ አቀራረብ ስለሚፈቅደው አካል እና የአፈፃፀም ሥርዓት

1/ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በአንዱ የመክፈል አቅም የሌለው መሆኑን ገልጾ ጥያቄውን ለመምሪያው ወይም ለጽ/ቤቱ የግብር አወሳሰን፣አሰባሰብና ክትትል ዋና ሥራ ሂደት ሲያቀርብ እና ምክንያቱ ተቀባይነት ሲያገኝ በዚህ መመሪያ በተገለጸው ሁኔታ የሚስተናገድ ይሆናል፤

2/ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ከሆነ የግብር አወሳሰን፣አሰባሰብና ክትትል ዋና ሥራ ሂደት አስተባባሪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ባለው መሰረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት ሊፈቀድ ይችላል፤

3/ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት በድጋሜ የቀረበ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ከሆነ የመምሪያው ወይም የጽ/ቤቱ ኃላፊ የሚፈቅድ ይሆናል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ፣በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአንቀጽ 10 መሠረት ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የታክስ ከፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ በመምሪው ወይም በጽ/ቤቱ ለሥራው አግባብነት ያለው የታክስ ዕዳ ክትትል ባለሙያ ወይም ይህን እንዲከታተል ውክልና የተሰጠው ባለሙያ የስምምነት ውል በማዘጋጀት ለሥራ ሂደት አስተባባሪው አቅርቦ እንዲፈረም ያደርጋል፤

5/ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል በ3 ኮፒ ተዘጋጅቶ ዋናው ኮፒ ከማህደር ጋር ይያያዛል፣ 2ኛው ኮፒ ለግብር ከፋዩ ይሰጣል፣ 3ኛው ኮፒ በግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የሥራ ሂደት በዕዳ ክትትል ባለሙያ ወይም የሚመለከተው ባለሙያ ለቀጣይ ክትትል ሥራ የሚያዝ ይሆናል፤

6/ በክፍያ ጊዜ ስምምነት ውሉ መሠረት ክፍያ የሚፈጸምበት ቀን በበዓላት ወይም በእረፍት ቀናት ላይ ከዋለ ክፍያው በቀጣዩ የስራ ቀን ይሆናል፤

7/ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የጳጉሜ ወር የነሐሴ ወር አካል ሆኖ ይቆጠራል፤

8/ የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የሥራ ሂደት አስተባባሪ የክፍያ ጊዜ ስምምነት የገቡ ታክስ ከፋዮች የክፍያ ስምምነት የተገባበትን የታክስ ዓይነት፣ የታክስ ዘመን፣ ዋና ታክስ ፣ መቀጫ እና ወለድ፣ በቅድሚያ የተከፈለ ገንዘብ መጠን፣ ስምምነት

የተገባበት ቀን እና የመክፈያ ጊዜ ያካተተ ዝርዝር መረጃ ሪፖርት በየወሩ እያዘጋጀ ለገቢዎች ቢሮ ለግብር አወሳሰን፣አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት ይልካል።

12. የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል ግዴታን አለመፈጸም

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ በውሉ መሠረት በየወሩ ካልከፈለ ታክስ ከፋዩ ክፍያውን ካቆመበት ጊዜ አንስቶ ያልተከፈለዉን ቀሪ ክፍያ እና ቀሪ መቀጫ ተሰልቶ በሙሉ እንዲከፍል በገቢዎች ቢሮ የግብር አወሳሰን፣አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት በታክስ ህጉ መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይችላል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ክፍያ ያቋረጠው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ አቋርጦት የነበረውን ታክስ በስምምነት ውል ጊዜ ውስጥ ያልከፈለውን ወራት አጠቃሎ እና የወጡ ወጪዎችን ጨምሮ የከፈለ ከሆነ የስምምነቱ ውል ሳይሰረዝ እንዲቀጥል ይደረጋል።

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ስራ ላይ በነበረዉ መመሪያ ተቀባይነት አግኝቶ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዚሚያ ተፈቅዶ በስምምነት ውሉ መሰረት በመከፈል ላይ ያለ የታክስ ዕዳ በነበረው መመሪያ መሠረት ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል።

14. ስለተሻሩ መመሪያዎች

በስራ ላይ የነበረው መመሪያ ቁጥር ገባ 11/2003 ስለ ክፍያ ጊዜ ስምምነት የተገለጹ አንቀጾች እና በተለያየ ጊዜ ለአፈጻጸም የተላለፉ ሰርኩላሮች በዚህ መመሪያ የተተኩ ስለሆነ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

15. <u>መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>

1/ ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ከነሀሴ 1 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ነው፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተገለጸው ቢኖርም፣ ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በአስተዳደር ተቋሙ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

ባህር ዳር

ብዙአየሁ ቢያዝን ይዘንጋው

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ